**በጉምሩክ ኮሚሽን**
**የአዲስ አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት**
**CUSTOMS COMMISSION**
**ADDIS ABABA KALITI CUSTOMS BRANCH OFFICE**
**የሥራ አስኪያጅ ጽ/ቤት የውስጥ ማስታወሻ**

ቁጥር፡ ስ/አ/ጽ/ቤት 100/12

ቀን:04/07/2012 ዓ.ም

ለ፡- የንግድ ገቢ ዕቃዎች አወጣጥ የስራ ሂደት
ለ፡- ወጪና ንግድ ያልሆኑ የገቢ ዕቃዎች የስራ ሂደት
ለ፡- ኢስተርን ኢንዱስትሪ ፓርክ የጉ/ሥ/ሥ/ አ/የስራ ሂደት
ለ፡- ኢንተለጀንስና ኮንትሮባንድ ክትትል የሥራ ሂደት
ለ፡- ቦሌ ለሚ ኢንዱስትሪ ፓርክ የጉ/ሥ/ሥ/ አ/የስራ ሂደት
ለ፡- ለቡ ኢንዱስትሪ ፓርክ

ከ፡- ስራ አስኪያጅ ጽ/ቤት
አ.አ. ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት

ፍቃዱ አማረ /ተወካይ/

ጉዳዩ፡- የኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ቁጥር 1186/2012 ተግባራዊ እንዲደረግ ስለማሳወቅ፤

ከጉምሩክ ኮሚሽን በቁጥር 6/0559/12 በቀን 03/07/2012 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የህዝብ ተወካዮች ም/ቤት የኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ቁጥር 1186/2012ን የካቲት 5 ቀን 2012 ዓ.ም ማጽደቁን ተከትሎ በገቢዎች ሚኒስቴር በኩል የካቲት 06 ቀን 2012 ዓ.ም በቁጥር 3.0/191/12 በተጻፈ ደብዳቤ አዋጁ በአገር ውስጥ ኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ምርቶች ማምረት ላይ በተሰማሩ ግብር ከፋዮች ላይ አዋጁ ከጸናበት ከየካቲት 6ቀን 2012 ዓ.ም ጀምሮ ተግባራዊ እንዲደረግ ተላልፏል፡፡

ስለሆነም ከላይ በተገለጸው አዋጅ ቁጥር 43 መሠረት ከጸናበት ቀን ጀምሮ የባንክ የውጭ ምንዛሬ ፈቃድ ተሰጥቶባቸው ወደ ሀገር የሚገቡ ዕቃዎች በአዲስ አዋጅ መሠረት እንዲስተናገዱ እንዲሁም አዋጁ ከጸናበት ቀን በፊት የውጪ ምንዛሬ ፍቃድ የተሰጠባቸው ዕቃዎች በተመለከተ ከየካቲት 6 ቀን 2012 ዓ.ም ጀምሮ በሚታሰብ ስድስት ወር ጊዜ ውስጥ ዕቃዎቹ ተጠቃለው ወደ ሀገር ውስጥ መግባታቸው እየተረጋገጠና በጉምሩክ አሰራር ኮድ/Extended procedure code/ 4500 እየተመዘገቡ በቀድሞው የኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ መሰረት እንዲስተናገዱ እንዲደረግ  በተላከው መሠረት እንዲፈጸም እያሳሰብኩ ለአፈጻጸም ይረዳችሁ ዘንድ የተላከው 1 ገጽ ደብዳቤ አባሪ በማድረግ የተላከ መሆኑን አሳውቃለሁ፡፡

N.B በገቢዎች ሚኒስቴር በኩል የተላለፈውን የአዋጁን አማርኛና እንግሊዘኛ ቅጂ ለአፈጻጸም በተቋሙ መረጃ ቋት
/lLocal sare/አድራሻ //10.12.0.8 ላይ ሳጥን Tariff classification & Origin/ Tariff classification
ሳጥን ውስጥ የኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ቁጥር 1186-2012 በሚል ርዕስ ተደራሽ ተደርገዋል፡፡

ከሠላምታ ጋር

ግልባጭ
ለ፡- ም/ስራ አስኪያጅ (አምራች ወጪና ሌሎች ባለጉዳዮች)
ለ፡- ም/ስራ አስኪያጅ (የንግድ ገቢ ዕቃዎች ኦፕሬሽን)
ለ፡- ም/ስራ አስኪያጅ (ህግ ተገዥነት)
ለ፡- ጉምሩክ አቤቱታ አጣሪ ጽ/ቤት
ለ፡- ደህረ-ዕቃ አወጣጥ የስራ ሂደት
ለ፡- ደንበኞች ትምህርትና ድጋፍ የስራ ሂደት
አ.አ. ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት

# በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የጉምሩክ ኮሚሽን
# THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
# CUSTOMS COMMISSION


ቀን መጋቢት 03 2012
Date
ቁጥር 6/0559/12
Ref.No.

የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ለሚፈጸምባቸው ቅ/ጽ/ቤቶች በሙሉ
<u>በያሉበት</u>

ለጉምሩክ ሥራ አመራር ሥርዓት ፕሮጀክት ጽ/ቤት
<u>ጉምሩክ ኮሚሽን</u>

ጉዳዩ፡- <u>የኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ቁጥር 1186/2012 ተግባራዊ እንዲደረግ ስለማሳወቅ</u>፡፡

የኢፌዲሪ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ቁጥር 1186/2012ን የካቲት 5 ቀን 2012 ዓ.ም. ማጽደቁን ተከትሎ በገቢዎች ሚኒስቴር በኩል የካቲት 06 ቀን 2012 በቁጥር 3.0/191/12 በተጻፈ ደብዳቤ አዋጁ በአገር ዉስጥ ኤክሳይዝ ታክስ የሚከፍልባቸዉን ምርቶች ማምረት ላይ በተሰማሩ ግብር ከፋዮች ላይ አዋጁ ከፀናበት ከየካቲት 6 ቀን 2012 ጀምሮ ተግባራዊ እንዲደረግ ተላልፏል፡፡

በመሆኑም ከላይ በተገለፀው አዋጅ ቁጥር አንቀጽ 43 መሠረት አዋጁ ከፀናበት ቀን ጀምሮ የባንክ የዉጭ ምንዛሪ ፈቃድ ተሰጥቶባቸው ወደ አገር የሚገቡ እቃዎች በአዲሱ አዋጅ መሠረት እንዲስተናገዱ እንዲሁም አዋጁ ከፀናበት ቀን በፊት የውጭ ምንዛሪ ፍቃድ የተሰጠባቸው እቃዎች በተመለከተ ከየካቲት 6 ቀን 2012 ዓ.ም. ጀምሮ በሚታሰብ ስድስት ወር ጊዜ ውስጥ እቃዎቹ ተጠቃለው ወደ ሀገር መግባታቸው እየተረጋገጠና በጉምሩክ አሰራር ኮድ /Extended Procedure Code/ 4500 እየተመዘገቡ በቀድሞው የኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ መሠረት እንዲስተናገዱ እናሳስባለን፡፡

በገቢዎች ሚኒስቴር በኩል የተላለፈዉን የአዋጁን አማርኛና እንግሊዘኛ ቅጅ ለአፈጻፀም በተቋሙ መረጃ ቋት /Local share/ አድራሻ <u>\\10.12.0.8</u> ላይ <u>Tariff Classification&Origin/ Tariff Classification</u> ሳጥን ውስጥ <u>የኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ቁጥር 1186-2012</u> በሚል ርዕስ ተደራሽ ተደርጓል፡፡

ከሠላምታ ጋር

አዘዘው ጫኔ አበበ
የጉምሩክ ኦፕሬሽን
ዘርፍ ምክትል ኮሚሽነር

ግልባጭ፡-

- ለኢ.ፌ.ዴ.ሪ.ገንዘብ ሚኒስቴር
- ለኢ.ፌ.ዴ.ሪ.ገቢ.ዎች ሚኒስቴር
- ለኢትዮጵያ የጉምሩክ አስተላላፊዎች ሞያ ማህበር
- ለኢትዮጵያ ፍሬት ፎርዋርደርስ ኤንድ ሺፒንግ ኤጀንትስ አሶሴሽን
  <u>አዲስ አበባ</u>
- ለጉምሩክ ኮሚሽን ጽ/ቤት
- ለጉምሩክ ህግ ተገዥነት ዘርፍ
- ለታሪፍ ምደባና ስሪት አገር አወሳሰን ዳይሬክቶሬት
  <u>ጉምሩክ ኮሚሽን</u>




☎ +251 116 62 98 00
Fax +251 116 62 98 19
✉ 2559
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ
Addis Ababa,Ethiopia